# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 241 ታህሳስ 18 2005 ገጽ 1


**ንቅናቄያችን ግንቦት 7 ወያኔ ገንብቻለሁ ብሎ የሚኮፈስበትን የፍርሃት ግምብ ደርምሰው ለነጻነታቸው ሲሉ ውድ የህይወት ዋጋ ለመክፈል በግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ዙሪያ መሰባሰባቸውን ይፋ ያደረጉ ወጣቶች የተነሱለትን ክቡር አላማ ያደንቃል። በዚህም ምክንያት ለነጻነቱ ቀናኢ ለሆነው ህዝባችን ያቀረቡትን የትግል ጥሪ ወቅታዊነት ሁሉም እንዲረዳው የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በቡሬ ግንባር የሚገኘው የኢትዮጵያ ሰራዊት እርስ በርሱ ተዋጋ

በቡሬ ግንባር ልዩ ስሙ ማንዳ እየተባለ በሚጠራዉ ቦታ የሰፈረዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ካለፈዉ ማክሰኞ ሌሊት እስከ ረቡዕ እኩለቀን ድረስ በዘለቀ የእርስ በእርስ ዉግያ ማድረጋቸዉን ኢሳት ቴሌቪዥን የመከላከያ ሚኒስትር ምጮችን ዋቢ አድርጎ ዘገበ። በዚህ ዉጥረቱና ዉዝግቡ አሁንም ድረስ እንዳልረገበ በሚነገርለት ግጭት 40 ወታደሮች መሞታቸውንና ከ39 በላይ መቁሰላቸውን ከማንዳ ሆስፒታል የተገኘ መረጃ ያመለካተ ሲሆን፣ ሆስፒታል ሳይደረሱ የሞቱ፣ ወደ መቀሌ ሆስፒታል በሄሊኮፕተር የተወሰዱ ወታደራዊ አዛዦች መኖራቸውንም ለማወቅ ተችሎአል። ከሞቱት ወታደሮች ዉስጥ 15ቱ ወታደሮች የሞቱት ወዲያዉኑ ሲሆን 12ቱ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዉ ለሞት ሲያጣጥሩ በአይናቸው ማየታቸውን አንድ ስማቸውም ድምጻቸውም እንዳይተላለፍ የጠየቁ ሆስፒታል ውስጥ የሚሰሩ ነርስ ተናግረዋል።

የወያኔ ከፍተኛ ከፍተኛ ወታደራዊ ባለስልጣናት የእርስ በርስ ግጭቱን ለማስቆም በሄሊኮፕተር እየተንቀሳቀሱ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የእርስ በርስ ጦርነቱ እንደተጀመረ በማንዳና በአካባቢው የሚኖረዉ ህዝብ ኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት የጀመሩ መስሎት አካባቢዉን ለቅቆ እንደወጣ ለማወቅ ተችሏል።

የዚህን የብዙ ወታሮችን ህይወት የቀጠፈዉን ግጭት መንስኤ በትክክል ለማወቅ የልተቻለ ሲሆን አንዳንድ ወገኖች ግጭቱ በህወሀት ወታደራዊ ባለስልጣናት መካከል የተፈጠረ አለመግባባት ዉጤት ነዉ ሲሉ ሌሎች ወገኖች ደግሞ በህወሀት ደጋፊ ወታደሮችና በተቀረው ሰራዊት መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ነው ይላሉ። የቡሬ ግንባር ዋና እዝ መቀሌ የሚገኝ ሲሆን፣ በሰሜን እዝ አዛዥ ጄነራል ሳአረ መኮንን እንደሚመራ ይታወቃል።ቡሬ ግንባር የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከባድመ ቀጥሎ ሀይሉን በብዛት ያሰማራበት ቦታ መሆኑ ይታወቃል። ኢሳት በቅርቡ በሰሜን ግንባር የተመደበን አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል በማናገር በሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ችግር መዘገቡ ይታወሳል።

በሌላ ዜና ደግሞ በአካባቢው ለሚንቀሳቀሰው የአፋር ጋድሌ ሚሊሺያ ሀይል ወጣቶችን ትመለምላላችሁ የተባሉ የሚሊሺያው ወታዳራዊ አዛዥ የሆኑት የኮሎኔል ሙሀመድ አህመድ 4 የቅርብ ዘመዶች ተይዘው ታስረዋል። በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት መንገሱንና መንግስትም ካለፉት ሁለት ሳምንታት ጀምሮ በርካታ ወታደሮችን ማስፈሩን መዘገባችን ይታወሳል።

## ለነጻነታቸው ሲሉ ውድ የህይወት ዋጋ ለመክፈል በግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ዙሪያ መሰባሰባቸውን ይፋ ያደረጉ ወጣቶች የተነሱለትን ክቡር አላማ እንደሚያደንቅ ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ገለጠ

የግንቦት ሰባት የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ ገንብቻለሁ ብሎ የሚኮፈስበትን የፍርሃት ግምብ ደርምሰው ለነጻነታቸው ሲሉ ውድ የህይወት ዋጋ ለመክፈል በግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ዙሪያ መሰባሰባቸውን ይፋ ያደረጉ ወጣቶች የተነሱለትን ክቡር አላማ እንደሚያደንቅ ባወጣው የንቅናቄው ሳምንታው ርእሰ አንቀጽ ላይ አስታወቀ።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ "ብሶት የወለደው" ወያኔ ብሶተኞችን እየፈለፈለ ነው በሚል ርእስ ባወጣው በዚሁ ሳምንታዊ ርእሰ አንቀጹ በአገራችን ውስጥ የነበረው ብልሹ አስተዳደር በፈጠረው ኢፍትሃዊነት ብሶት አርግዞ ለድል ያበቃውን ጠመንጃ እንደመዘዘ በኩራት የሚደሰኩረው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፡ የመንግሥት ሥልጣንን የሙጥኝ በማለት በህዝባችን ላይ እየፈጸመ ባለው ሰቆቃ ተማርረው በተራቸው ብሶት አርግዘው ጠመንጃ ለማንሳት የሚገደዱ ሃይሎችን በየቀኑ እየፈለፈለ መሆኑ በተግባር እየታየ ነው ብሉአል ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በርእሰ አንቀጹ መጨረሻ ላይ ለነጻነቱ ቀናኢ ለሆነው ህዝባችን ወጣቶቹ ያቀረቡትን የትግል ጥሪ ወቅታዊነት ሁሉም እንዲረዳው ንቅናቄው የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል ብሉአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የመለስ ራዕይ የሚባል ነገር የለም ሲል ስብሐት ነጋ ተናገረ፣ በአዲስ አበባ መለስን የሚያወድሱ ፖስተሮች እየተነሱ መሆናቸው ታወቀ

አንጋፋዉ የህወሀት መስራችና መሪ ስብሐት ነጋ የመለስ ራዕይ የሚባለው ነገር ትክክል እንዳልሆነና የወያኔ ራዕይ የጋራ ራዕይ መሆኑን በያዝነዉ ሳምንት አጋማሽ አዲስ አበባ ዉስጥ ለንባብ ለበቃው ሰንደቅ ጋዜጣ በሰጠዉ ቃለ ምልልስ መናገሩን የአዲስ አበባ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ስብሐት ነጋ ይህንን የተናገረዉ ብዙዎችን ግራ ያጋባዉንና በቅርቡ ኢትዮጵያ ዉስጥ የወያኔ አገዛዝ የሰጠዉን የሦስት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች ሹመት አስመልከቶ የቀረበለተን ጥያቄ ሲመልስ ነዉ። ስብሐት ነጋ እሱ እራሱ በፈጠረዉ ህወሀት ዉስጥ ይህ ነዉ ተብሎ የሚነገር ስልጣን ባይኖረዉም ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ ግን ህወሀት ዉስት በተፈጠረዉ የመሪ እጦትና አለመተማማን የተነሳ ተደማጭነቱ እየጎላ መጥቷል። በቅርቡ በየመገናኛ አዉታሩ አንደተስተዋለዉ ደግሞ ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ በነበሩት ሁለትና ሦስት ወራት ከፍተኛ ተሰሚነት ነበረዉ በረከት ስምኦን ድምጹ እየጠፋ ስብሐት ነጋ የኮከብ ተዋናይነቱን ቦታ እየያዘ መምጣቱ ይታወቃል።

አንጋፋዉ የህወሀት አባል ስብሐት ነጋ ሦስት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮችን መሾም ሕገ-መንግስቱን አይጥስም ወይ ተብሎ የተጠየቀዉን ጥያቄ ሲመለስ. . . . የሦስት ምክትል ጠ/ሚኒስትር መሾም ያስፈለገው ክፍት የአመራር ቦታ ስለነበር እንደሆነ ተናግሮ ሹመቱ መደረግ የነበረበት ነገር ነዉ ካለ በኋላ መልሱን በመቀጠል እኔ የማውቀው ነገር የለም ሆኖም ሕገ-መንግስቱ ተጥሷል ከተባለ ያለው አማራጩ ሕገ-መንግስቱን ማሻሻል ወይንም ሌላ አማራጭ መፈለግ ነዉ እንጂ አዲሱ አደረጃጀት መቀጠል አለበት የሚልና የህወሀትን ህገወጥነትና ጋጠወጥነት በግልጽ የሚያሳይ አስነዋሪ መልስ ሰጥቷል። ስብሐት ነጋም ሀነ ሦስቱን ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች የሾሙት የህወሀት ባለስልጣኖች አሁን ተፈጠረ የተባለዉ የአመራር ክፍተት አንዴት በመለስ ዜናዊ የሃያ አንድ የልጣን ዘመን እንዳልተፈጠረ ከህዝብ የቀረበላቸዉን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል የትግል ሜዳ መሃል አገርን ጨምሮ ወያኔ ባለበት ሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች መሆኑ ተዘገበ

የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል በሚል ስያሜ መመስረቱን ድርጂቱ በድረ ገጹ ላይ ባወጣው መግለጫ ያሳወቀ ሲሆን ይህን መግለጫ ተከትሎም በርካታ የዜና አውታሮች ሲዘግቡት መቆያታቸው ይታወሳል። ከዚሁ ዘገባ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በትናንትናው እለት ስርጪቱ ከግንቦት 7 ሃይል ቃል አቀባይ ታጋይ ዜና ጉታ ጋር ቃለ ምልልስ ያደረገ ሲሆን፣ በዚሁ ቃለ ምልልስ ላይ ቃል አቀባዩ እንደገለጹት የዝባዊ ሃይሉ ራእይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሉአላዊ የስልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠባት ጠንካራ ኢትዮጵያን እውን ሆና ማየት ነው ብለዋል።

ቃል አቀባዩ ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት የንቅናቄው ስም ግንቦት ሰባት የተባለበት ዋነኛ ምክንያት በ1997 ምርጫ ወቅት ግንቦት ሰባት ቀን የኢትዮጵያዊያን ድምጽ ባደባባይ በጉልበት የተነጠቀበት በመሆኑ፣ ቀኑ በኢትዮጵያዊያን ልዩ ቦታ የሚሰጠውና እለቱም የኢትዮጵያ ህዝብ ዘረኛውን የወያኔ አገኣዛዝ ፍጹም እንደማይፈልግ የገለጸበት እንዲሁም ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ዝግጁነቱን ያረጋገጠበት ቀን በመሆኑ ነው ብለዋል።

የግንቦት ሰባት ሃይልን አሁን መመስረት ለምን አስፈለገ በሚል የኢሳት ጋዜጠኛ ለታጋይ ዜና ጉታ ላቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል።

የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ቃል አቀባይ የሆኑት ታጋይ ዜና ጉታ ወያኔን በትጥቅ ትግል ለማስወገድ በምድር ላይ እየተንቀአሳቀሱ ካሉ ሃይሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑንና፣ ከነኚሁ ሃይሎች ጋር በጋራ ለመስራት አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታ ማጠናቀቃቸውን እንዲሁም የዚህ ሃይል የትግል ሜዳ መሃል አገርን ጨምሮ ወያኔ ባለበት ሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ነው በማለት፣ በዚሁ ቃለ ምልልስ ላይ አብራርተዋል። ቃል አቀባዩ ለኢሳት እንደገለጡት የግንቦት 7 ሃይል ከትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ወይም ደሚት፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህና እኩልነት ግንባር፣ ከጋምቤላ ህዝብ ነጻነት ንቅናቄ፣ ከቤንሻንጉል ህዝብ ነጻነት ንቅናቄ እንዲሁም የአማራ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ከተባሉት ድርጅቶች ጋር በጥምረት ለመስራት አስፈላጊው ዝግጅት አጠናቋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ብሶት የወለደኝ እያለ የሚመጻደቀው ወያኔ ብሶተኞችን እየፈለፈለ ነው

በአገራችን ውስጥ የነበረው ብልሹ አስተዳደር በፈጠረው ኢፍትሃዊነት ብሶት አርግዞ ለድል ያበቃውን ጠመንጃ እንደመዘዘ በኩራት የሚደሰኩረው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፡ የመንግሥት ሥልጣንን የሙጥኝ በማለት በህዝባችን ላይ እየፈጸመ ባለው ሰቆቃ ተማርረው በተራቸው ብሶት አርግዘው ጠመንጃ ለማንሳት የሚገደዱ ሃይሎችን በየቀኑ እየፈለፈለ መሆኑ በተግባር እየታየ ነው።

ወያኔ የድጋፍ መሠረቴ ነው ከሚለው የትግራይ ክልል ውስጥ የወጣው "**የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት**" ወይም **ዴሚት** በሚል ምህጻረ ቃል ከሚጠራውና በርካታ የትግራይ ወጣቶችን ማሰባሰብ ከቻለ ድርጅት ጀምሮ "በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የብሄር እኩልነት ካባ አከናንቤያችኃለሁ" ብሎ ወያኔ ከሚመጻደቅባቸው ህዝቦች አብራክ የወጡ **የኦሮሞ፣ የኦጋዴን፣ የቤነሻንጉል፣ የጋምቤላ፣ የአፋርና የደቡብ ህዝቦች** የዚህን ዘረኛ ሥርዓት እብሪትና ጥጋብ አስተንፍሰው የተዋረደውን ክብራቸውን ለማስመለስ መሳሪያ አንስተው መፋለም ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

በወያኔ የዘር ፖለቲካ ከማለዳው ጀምሮ የጥቃት ሰለባ የሆነውና እንደ ባዕድ ወራሪ በሰላም ከየሚኖርባቸው ክልሎች ታድኖ የሚባረረው አማራም "በዘር መደራጀት ከጥቃት የሚያድን" ከሆነ በሚል ቁጭት ተደራጅቶ የትጥቅ ትግሉን ጎራ መቀላቀሉን አስታዉቋል። በብሄር እኩልነት ስም በየክልሉ ለተሾሙ ምስለኔዎች በታኮነት የተመደቡ ዘረኞች በህዝባችን ስም እየማሉና እየተገዘቱ የሚያደርሱት ግፍ አስመርሯቸው ጠመንጃ ካነሱ ከነዚህ የብሄር ድርጅቶች በተጨማሪ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ላለፉት 12 አመታት ከወያኔ ጋር የሽምቅ ውጊያ እያካሄደ ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርም የተፈጠረው ወያኔ በህዝባችንና በአገራችን ላይ በሚፈጽማቸው ወንጀሎች ብሶት ባረገዙ ዜጎች መሆኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ የለም።

ሰሞኑን ደግሞ የወያኔን ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ በትጥቅ ትግል ለማስወገድ በአገር ወዳድና ለህዝብ ተቆርቋሪ በሆኑ ዜጎች ስብስብ፤ ወጣቶችና፣ ምሁራን የተሞላ ድርጅት ማቋቋሙን ለህዝብ ይፋ ያደረገው "**የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል**" ካሰራጨው መግለጫ መረዳት እንደተቻለው፤ ወያኔ ድርድርና እርቅ የማይገባው፣ ትዕግስትን እንደፍራቻ፣ እርቅ አሳቢነትን ደግሞ እንደ ሞኝነት የሚቆጥር በዚህም ስሌት ሕዝብን ለዘላላም እየረገጠና እየዘረፈ ለመግዛት ቆርጦ የተነሳ እኩይ ኃይል በመሆኑ ወያኔን ሊገባው በሚችል ብቸኛ ቋንቋ በማነጋገር የአገዛዝ ዕድሜውን ለማሳጠር ቆርጦ ብረት ያነሳ ሃይል ተፈጥሯል።

ግንቦት7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ሲያስጠነቅቅ እንደኖረው ፋሽስት ጣሊያን ሞክራ ባልተሳካላት የመንገድና የህንጻ ግንባታዎች ተደልሎ ወይም ከግማሽ በላይ የሆነውን ህዝባችንን ለረሃብ በዳረገ ወያኔ ግን ልማትና እድገት ብሎ በሚጠራው ለውጥ ተታልሎ ክብሩንና ነጻነቱን አሳልፎ በመስጠት እስከወዲያኛው ለወያኔ ባሪያ ሆኖ ለመገዛት የተዘጋጀ ህዝብ የለም ብሎ ያምናል።

ወያኔ ጥጋብ በወለደው እብሪቱ በማንአለብኝነት የህዝብን መብትና ነጻነት ረግጦ በአፈና ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች አለኝታየ በሚላቸው የፖሊስ፣ የደህንነትና ወታደራዊ ኃይሎች እስከ መጨረሻው አጠናክር ለመቀጠል የሚችል አድርጎ ያስባል። በዚህም ምክንያት እስካፍንጫው ባስታጠቀው ወታደር ብዛትና በነዋሪው ቁጥር ልክ ህዝብ መሃል ባሰማራው ሰላዮች የተገነባው የፍርሃት ግምብ የሚናድም መስሎ አይታየውም። ሃቁ ግን በግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል የተሰባሰቡ ወጣቶችም ሆኑ ወያኔን በአራቱም የአገራችን ማዕዘናት ለመግጠም ጠመንጃ ያነሱ ሃይሎች ወያኔ ህዝባችንን ሊያስፈራራ የሚችልበትን ሁሉ በጣጥሰው ለመውጣት ምንም ችግር የሌለባቸው መሆኑን ነው።

ንቅናቄያችን ግንቦት 7 ወያኔ ገንብቻለሁ ብሎ የሚኮፈስበትን የፍርሃት ግምብ ደርምሰው ለነጻነታቸው ሲሉ ውድ የህይወት ዋጋ ለመክፈል በግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ዙሪያ መሰባሰባቸውን ይፋ ያደረጉ ወጣቶች የተነሱለትን ክቡር አላማ ያደንቃል። በዚህም ምክንያት ለነጻነቱ ቀናኢ ለሆነው ህዝባችን ያቀረቡትን የትግል ጥሪ ወቅታዊነት ሁሉም እንዲረዳው የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## አደናጋሪው የወያኔ አገዛዝ አቡነ መርቆርዮስ ቢመለሱ አልቃወምም ማለቱ ተሰማ

እንደ እስስት ራሱን በመቀያየርና ለአንዲት ቀንም ቢሆን ስልጣን ላይ እስካቆየው ድረስ ሊከተል ስለሚችለው ነገር ቦታ ሰጥቶ የማያውቀው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ በግፍ አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ ያስገደዳቸውንና በውጪ ሃገር በስደት ባሉበት ሁኔታ እንኳን ሳይቀር ግፍ ሲፈጽምባቸው የቆዩትን አቡነ መርቆሪዮስ ወደ ኢትዮጵያ ቢመለሱ አልቃወምም ማለቱን ሰንደቅ በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ ዘግቡአል። ቀደም ብሎ ከበርካታ ሳምንታት በፊት የሃገሪቱ አሻንጉሊት ፕሬዘዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ አቡነ መርቆሪዮስን በሚመለከት ከ ቪ ኦ ኤ ጋር እርስ በእርሱ የሚጋጭና አሳፋሪ ቃለ ምልልስ ማድረጉ ይታወቃል።

እንደ ሰንደቅ ዘገባ የአገዛዙ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መንግስት በህገ-መንግስቱ መሠረት በሃይማኖቶች የውስጥ ተግባር ጣልቃ መግባት ስለማይችል አቡነ መርቆርዮስ ይመለሱ ወይም አይመለሱ የማለት ህገ-መንግስታዊ መሰረት የለውም፣ በኢትዮጵያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ፤ 4ኛው ፓትርያሪክ የነበሩት አቡነ መርቆርዮስ ይመለሱ ብሎ ካመነ መንግስት ተቃውሞ የለውም>> የሚል የሚገርምና የቅጥፈት መግለጫም ማውጣቱ ታውቋአል።

ሰንደቅ ጋዜጣ እንደዘገበው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አበበ ወርቁ መንግስት ለሰላምና ፀጥታ ሲባል የተጀመረውን እርቀ-ሰላምን ሲደግፍ መቆየቱን በመጥቀስ የፓትርያሪክ ምርጫው በሰላምና በመከባበር እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኗ ህግ፣ ደንብና መመሪያ እንዲፈፀም ፍላጎት እንዳለው ተናግሩአል ብሉአል። አያይዞም በሕገ-መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት ኃይማኖትና መንግስት የተለያዩ በመሆናቸው "እገሌ ሹም አገሌን ሻር" ብሎ የመወሰን ስልጣኑ ከሃያ አመታት በፊት አክትሟል በማለት ነጭ የሆነ ውሸትን ዋሽቱአል።

ይሄው ሆድ አደር የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በቅርቡ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በአሜሪካ የሚገኙት 4ኛው ፓትርያሪክ ብፁዕ አቡነ መርቆሪዮስ ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ በደብዳቤ መጠየቃቸውን በተመለከተ ተጠይቆ "ፕሬዝዳንቱ እንደ ግለሰብ ደብዳቤ ፅፈዋል። ምናልባትም ግለሰቦች በሚፈጥሩት ውዥንብር ገብተው፣ ጉዳዩ ወደ ብጥብጥ የሚሄድ መስሏቸው፣ እንዲህ ቢደረግ በሚል ግለሰባዊ እይታቸውን አንፀባርቀው ነበር። ነገር ግን በዚህ ስልጣን ላይ ሆነው ግለሰባዊ ዕይታም ቢሆን መስጠት የማይችሉ መሆኑን ወዲያው ተገንዝበው አርመዋል" በማለት የሚገርም መልስ ሰጥቱአል።

በተያያዘ ዜና ደግሞ ኢትዮጵያዊያንን በመከፋፈል አባዜ የተለከፈው ስብሃት ነጋ ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ በአገር ውስጥ ያለው ሲኖዶስ በኢትዮጵያ ያለውን የእስልምና አክራሪነት እንቅስቃሴን የውጩ ሲኖዶስ ሲደግፍ አለማውገዙ እንዳሳዘነው ተናግሩዋል። ስብሀት ነጋ ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ የአሜሪካው ሲኖዶስ የእስልምና አክራሪ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚደግፍ ይወራል፣ አገር ውስጥ ያለው ሲኖዶስም የቤተክርስቲያኒቱ ህልውና ቆርቁሮት ተነስቶ ይህን ድርጊት አላወገዘም። የእስልምና አክራሪነት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ደጋፊ ከሆነም መንግስት እርምጃ መውሰድ ነበረበት።" በማለት የተለመደውን መርዛማ የመከፋፈያ ቃለ ምልልሱን አድርጉአል።

ከዚህ ዘገባ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ባወጣው ዘገባው ስብሀት ነጋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሙስሊሙን የአንድ አመት እንቅስቃሴ አለማውገዟ በቤተከርስቲያኑዋ ህልውና ላይ የተቃጣ አደጋ እንደሆነ አድጎ ማቅረቡ በግልጽ በሙስሊሙና በክርስቲያኑ መካከል ግጭት ለመፍጠር ማሰቡን የሚያሳይ ነው በማለት አንድ ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉ የሀይማኖት አባት አስተያየታቸውን መስጠታቸውን ገልጡአል።

"የሙስሊሙ እንቅስቃሴ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ህልውና የሚነካ ለመሆኑ ማስረጃ የለም" ያሉት እኚሁ አባት፣ በባዶ ሜዳ እንድናወግዝ መጠየቃችን ከበስተጀርባው ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ከሙስሊሙ ጋር ለማጋጨት የታለመ ነገር መኖሩን ያሳያል ሲሉ አክለዋል።

"ለቤተክርስቲያናችን ህልውና አደጋ የሆነው የአቶ ስብሀትና ጓኞቻቸው መንግስት እንጅ ሙስሊሙ ወገናችን አይደለም፣ ሙስሊሙማ በሀይማኖታችን ጣልቃ አትግቡብን መሪዎቻችንን እኛ እንምረጥ መንግስት አይመረጥብን በማለት እየጮከ" በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል ብሉአል ኢሳት።

---

## ህወሃትን ፈጣሪም ሰውም ተፀይፎታል !

ህወሃት ጭካኔውን እንደ ጀግንነት፤ ድንቁርናውን እንደ እውቀት ቆጥሮት እኔ ብቻ ጀግና! እኔ ብቻ አዋቂ! ብሎ በትዕቢት አብጦ በማን አለበኝነት ታብዮ የኖረ ዘረኛ ቡድን ነው። የዚህ ቡድን ትዕቢት ልክና ወሰን የለውም። የትዕቢታቸው መገለጫም ብዙ ነው።"እኛ ከሌለን ኢትዮጵያን እንበትናታለን" ብለው የሚዘባትሉትን ማስታወስ ብቻ በቂ ነው። ይሄ የጨካኞች መገለጫ እንጂ የጀግና ጠባይ አይደለም። ጀግና አገር ይገነባል እንጂ አገር አይበትንም። ጀግና ለአገሩ አንድነትና ለህዝቡ ክብር ይዋደቃል እንጂ እኔ ከሌለው አገሪቷን አፈርሳታለው ብሎ አይዘባትልም። ህወሃቶች ከትእቢታቻው ላይ በወንድማማቾች መካከል ጥላቻን የመዝራት የረከሰ ስብዕናቸው ታክሎበት በሰውና በፈጣሪ ፊት የተጠሉ እንዲሆኑ ሁነዋል።መጽሃፍ ቅዱስም "እግዚአብሄር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ፤ በወንድማማቾች መካከል ጥላቻ የሚዘራውንም ነፍሱ አጥብቃ ትፀየፈዋለች" ይላል። ህወሃቶች የሚገለጹት በዚህ መልኩ ነው።ከዚህ ሌላ መልክ የላቸውም።

በእነዚህ በሰውና በፈጣሪ ፊት በተናቁና በተጠሉ ቡድኖች አማካኝነት በኢትዮጵያችን ላይ የተፈፀመውን ግፍ ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። አዎን በደል አይረሳም። በህወቶች የተፈፀመው በደል የማንረሳው የታሪካችን ህያው አካል ነው።ህወሃቶች በአገራችን ላይ የፈፀሙትን በደል ያላካተተ የኢትዮጵያ ታሪክ ጎዶሎ ነው። ህወሃት የኢትዮጵያ መጥፎ ገጽታዋ መገለጫ ነው።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን ! አገራችን እንዲህ ያለ መከራ ውስጥ የገባችው በህወሃቶች ክፋት ብቻ አይደለም፤ የእነርሱን ክፋት እያዩ ዝም በሚሉ ቅን ዜጎችም ጭምር ነው። ከሃያ ዓመት በላይ ፈረጀ ብዙ የሆኑ ግፎችን ተሸክመን ዝም በማለታችን "አህያ" ተብለን ተሰደብን እንጂ ያተርፍነው በጎ ነገር የለም። ዝም ማለት የህወሃቶችን እድሜ አራዝሞ ብዙሃኑ ጥቂቶችን ተሸክመው፤ ጥቂቶቹም ብዙሃኑን ተጭነው የሚኖሩባት አገር እንድትሆን ከማገዝ በቀር ለነፃነታችን የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የለም። እኛ ከአያት ቅደም አያቶቻችን የወረሰነውን በነፃነት የመኖር ልማድን ለዘረኞች አሳልፈን ሰጥተን ዝም የምንል አልባሌ ሰዎች ልንሆን አይገባም። የህወሃቶችን ግፍና በደል ተሸክመን እንኖር ዘንድ እኛ እርግማን ያለብንም ዜጎች አይደለንም።

ህወሃት ማለት በአገራችን ላይ የተተከለ መርገምት ማለት ነው።የመርገምትነቱም መገለጫ በዜጎች መካከል መለያየትንና አለመተማመንን ማስፈኑ፤ በሃይማኖቶች መካከልም እየገባ ግጭት ፈጥሮ የንጹሃን ደም በከንቱ እንዲፈስ ማድረጉ፤ንጹሃን ዜጎችን በሃሰት ከሶ ምናምንቴ ግለሰቦችን ምስክር አቁሞ የእድሜ ልክ እስራትና የሞት ፍርድ ፈርዶ ዜጎችን ማሰቃየቱ ጥቂቶቹ የመርገምትነቱ መገለጫዎች ናቸው። እርግጥ ነው ይህን እርግማን ተሸክመው ለመኖር የማይጎረብጣቸው እና የሂሊና ጥያቄ የሌለባቸው ደካማ ግለሰቦች ይኖራሉ። እነዚህ ትርፍራፊ ለቃቀመው ሆዳቸውን ከሞሉ፤ ጭላጭ አግኝተው ከተጎነጩ ሁሉም ሰላም ነው የሚሉ ሰው የመሆን ነገራቸውን ረስተው፤ ራሳቸውን አራት እግር ካላቸው አሳሞችና ፈረሶች ጋር ማመሳሰልን የመረጡ ናቸው። ይህ ምርጫ ግን ትክክል አይደለም። ይህም በራሱ ሌላ መርገምት ነው። ትግል የሚያስፈልገውም እንደነዚህ ዓይነቶቹ ራሳቸውን ከሰው ተራ ያወረዱትን ሰው ወደመሆን ደረጃ ከፍ ብለው እንደ ሰው እንዲያስቡ ለማደረግም ጭምር ነው።

እንግዲህ ለራሱ ክብር የሚሰጥ ዜጋ ይህን መርገምት ተሸክሞ ለመኖር እሺ አይልም። እንዲያውም መርገምቱን ከሥሩ ነቅሎ ወዲያ ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊም መሪም ይሆናል። ይህን መርገምት መዋጋት ግዜው የሚጠይቀው የቅን ዜጎች የሞራል ግዴታ ነው። በሌላ በኩል ህወሃትን እንደ መንግስት አይቶ ትዕዛዙን ለመቀበል እሺ ማለት ዘረኝነትንና ግፍን በጣም ጥሩ አድርጎ ማጠናከር ነው። ህወሃትን ለመሰለ ዘረኛ እና ዘራፊ ቡድን መታዘዝ ማለት የዘረኝነቱና የጥፋቱ ተባባሪ መሆን ማለት ነው። ማንኛውም መልካም ሰው ዘረኝነትንና ግፍን በሙሉ እስትንፋሱ የመቃወም የሞራል ግዴታ አለበት። ህወሃትን ሰው ብቻ ሳይሆን ፈጣሪም ተፀይፎታል።ፈጣሪ የተፀየፈውን አለመፀየፍ ከጥሩ ሰው ተርታ የሚያስቆም አይደለም።

በህወሃቶች አማካኝነት የብዙ ንጹሃን ዜጎች ደም በከንቱ ፈሷል። በእነዚህ ዘረኞች አማካኝነት አማሮች ናችሁ ተብለው ከኖሩበት ተነቅለው ወደ አገራችሁ ሂዱ ተብለው ሜዳ ላይ የተበተኑ ዜጎች ብዙ ናቸው። በኢትዮጵያችን ውስጥ ከታች እስከ ላይ እርከን ያሉ የመንግስት ስልጣኖች በሙሉ መሃይማን በሆኑ ህወሃቶች ተይዟል። በህወሃቶች አማካኝነት በጋምቤላ እና በኦጋዴን የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል፤በእነዚህ ቡድኖች አማካኝነት ከድሆች ጉሮሮ ተነጥቆ ከ11 ቢሊዮን ዶላር በላይ በውጭ አገር ባንኮች ውስጥ ተደብቋል። እንግዲህ እንዲህ ዓይነቶቹን የዘመኑ መርገምቶችን በሙሉ እስትንፋስ ለመቃወም አለመነሳት አሳፋሪ ነው።

በእነዚህ ዘረኞች አማካኝነት ሲፈፅሙ የኖሩ በደሎችን መቃወም የወቅቱ ትክክለኛ ተግባር ነው። ከሰሞኑ የግንቦት ሰባት ኃይል የሚባል ቡድን ካሁን ወዲያ ልቅሶው ያብቃ፤ የሚሰደዱ በአገራቸው ረግተው በሰላም ይኑሩ፤ ወጣቱ ተምሮ ድንጋይ ፈላጭ አይሁን፤ ዜጎች በብሄራቸው ብቻ ተለይተው ከኖሩበት ቀየ ተነቅለው ሜዳ ላይ አይጣሉ፤ በልማት ስም ዜጎች መድረሻ አይጡ ብለው ጋሻና ጦራቸውን አንስተዋል። የግንቦት ሰባት ንቅናቄም አገራችን ላይ የተተከለውን ህወሃት የተባለ መርገምት ነቅሎ ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል። ግንቦት ሰባት በኢትዮጵያችን ውስጥ ታሪካዊ እለት ነች። ኢትዮጵያዊያን በድምፃቸው መንግስታቸውን መምረጥ የሚችሉ መሆናቸውን ያሳዩበት እና የነፃነት ጎህ የፈንጠቀበት ዕለት ግንቦት ሰባት ነበረች። በሌላ በኩልም ግንቦት ሰባት ቃየላዊያን የብዙ አቤሎችን ደም ሊያፈሱ የተማማሉበት ዕለትም ነች። በዚህች ዕለት በተሴረው ሴራ የፈሰሰው ደም፤የወረደው እንባ፤ በወገኖቻችን ላይ የተፈፀመው ግፍ ትግላችንን ለመሰብሰብ በቂ ምክንያት ነው። ከዚያም ከዚህም ተጠራርቶ በዚህች እለት ዙሪያ ተሰባስቦ ትግሉን በሁሉም አቅጣጫ ማካሄድ ግዜው የሚጠይቀው የትግል ስልት በመሆኑ ከሰሞኑ የግንቦት ሰባት ህዛባዊ ኃይል ያስተላለፍውን ጥሪ ንቅናቄያችን አድንቆ ተቀብሎታል።

ህወሃቶች ከሃያ ዓመት በላይ አገሪቷን ሰባብረዋል፤ዜጎችን አዋርደዋል። ይሄን ሁሉ ዘመን ከዛሬ ነገ ይሻላሉ፤ ከዛሬ ነገ እንደ ሰው ልጅ ማሰብ ይጀምራሉ፤ ከዛሬ ነገ ከስህተታቸው ተምረው ይመለሳሉ በሚል እሳቤ ታግሰናል። እነርሱ ግን ትዕግስታችንን እንደ ፍርሃት፤ አርቆ አስተዋይነታችንንም እንደ ሞኝነት ቆጥረው የጭካኔ እጃቸውን ከጫንቃችን ላይ ለማንሳት እምቢ ብለው ቆይተዋል። ይሄ ግን ማብቃት አለበት።ማብቃት አለበት ስንል ደግሞ በማንኛውም መንገድ እየሄድን፤ እየወደቅንና እየተነሳን አስቸጋሪውን ጉዞ በአጭር ግዜ ጨርሰን ነፃነታችንን ለማወጅ የሚከፈለውን መሥዋእትነት ለመክፈል ዝግጁዎች መሆናችንን እያሳወቅን ነው።

የተከበራችሁ ወገኖቻችን! ኢትዮጵያችን የምትዋረደው ህወሃቶች በሚፈፅሙት ግፍ ብቻ አይደለም፤ የሚፈፀመውን ግፍ እያዩ ዝም በሚሉ ቅን ዜጎችም ጭምር ነው። ህወሃት የሰው ልጅ ይቅርና ፈጣሪ የተፀየፈው ቡድን ነው። ፈጣሪ የተፀየፈውን ትፀየፉት ዘንድ ግዜው ደርሷል፤ ዝምታው ይብቃ፤ፍርሃቱም ይሰበር። ዛሬውኑ ትግሉን ተቀላቀሉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## ለነጻነታቸው ሲሉ ውድ የህይወት ዋጋ ለመክፈል በግንቦት 7

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በንዲህ እያለ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንደሚደግፉና አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግም ንቅናቄአቸው ዝግጁ መሆኑን ዶር ብርሃኑ ነጋ የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ከኢሳት ራዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገልጸዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ትግል ለማድረግ ያለው እድል መዘጋቱ የመሳሪያ ትግል አማራጭነት አስፈላጊነት መሆኑን ያወሱት ዶር ብርሃኑ ነጋ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጂግ ወሳኝ ከሆነ ምእራፍ ላይ መድረሱን አውስተው ከዚህ በሁአላ የሚኖረውም ትግል መራርና ጠንከር ያለ ይሆናል ሲሉ በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው ገልጸዋል። የኢሳት ራዲዮ ከዶር ብርሃኑ ነጋ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ ሙሉ ዝግጂት በሚቀጥለው ሃሙስ ፕሮግራሙ እንደሚያቀርብ አስታውቁአል።

የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል መመስረቱንና ወደ ትጥቅ ትግልም መግባቱን ያስታወቀውና ኢትዮጵያዊያንም እንዲቀላቀሉት ጥሪ ያቀረበው ባለፈው አርብ እለት መሆኑ ይታወሳል።

## የመለስ ራዕይ የሚባል ነገር የለም ሲል ስብሐት ነጋ ተናገረ፣

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስብሐት ነጋ የፈጠረዉና ለረጂም ግዜ የመራዉ ህወሀት ህገ መንግስቱን በጣሰ መልኩ ሦስት ምክትል ጠ/ሚኒሰትሮችን መሾሙ በግልጽ እየታወቀና ሰብሐት ነጋ እራሱም ይህንን ትልቅ ስህተት ለማረም ህገ መንግስቱን እናሻሽላለን እያለ "እኔ ሥርዓት ከጣስኩ ከግንቦት 7፤ ከኦብነግና ከኦነግ በምን እለያለሁ" ብሎ መናገሩ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስርዐት የሚጥሰዉ ወያኔ አንጂ ስብሐት ነጋ በስም የጠቀሳቸዉ ድረጅቶች አይደሉም ሲሉ ብዙዎች አስተያት በመስጠት ላይ መሆናቸዉን የአዲስ አበባ ዘጋቢዎቻችን አክለዉ በላኩልን ዜና ገልጸዋል።

ይህ በንዲህ እንዳለ "ራዕይህን እናሳካለን"፣ "አባይን የደፈረ መሪ"፣ "ቃልህን እንጠብቃለን" እና የመሳሰሉ የውዳሴ ቃላት ጋር የመለስን ምስል የያዙና በውድ ዋጋ የተሰሩ ፖስተሮች አዲስአበባ ከተማን ጨምሮ ክልሎችን ከማጥለቅለቃቸው ጋር ተያይዞ ግንባሩ ባልተለመደ ሁኔታ ግለሰብ ወደማምለክ ደረጃ ማሽቆልቆሉ በራሱ አባላት ጭምር ከፍተኛ ትችትን አስከትሎበታል ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቮዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ ሰሞኑን በአዲስአበባ በተለይ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

........................................................................................................................................

## ኦሮሚያ ዉስጥ ዳኞች በብዛት ስራቸዉን እየለቀቁ መሆኑ ተነገረ

ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በተለያየ ደረጃ በዳኝነት ስራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ስራችንን ከፖለቲካ ተጽእኖ ነጻ በሆነ መንገድ ለመስራት አልቻልንም በሚል በብዛት ስራቸዉን እየለቀቁ መሆኑን ከወደ ኦሮሚያ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ባለፉት ሁለት አመታት ብቻ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በዳኝነት ስራ ላይ የሚያደርገዉን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በመቃወም ከ100 በላይ ዳኞች ስራቸውን የለቀቁ ሲሆን በያዝነው አመት ደግሞ ይህ ቁጥሩ በእጥፍ ሊጨምር እንደሚችል በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ።

ከአንድ ወር በፊት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩት አቶ ታደለ ነጊሾና አቶ ሰይድ ጁንዲን ስልጣናቸውን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ እንዲለቁ ከተደረጉ በሁዋላ፣ ችግሩ መባባሱ ተገልጾአል።ሁለቱ ፕሬዚዳንቶች አሁን ባለው የፌደራል ስርአትና በክልሉ መንግስት ላይ አመኔታ ስለሌላቸው ከስልጣን እንዲለቁ መደረጋቸውን ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉ ዳኞች ለኢሳት ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር140/99 መሠረት ፕሬዚዳንቱና ምክትላቸዉ ከስልጣን የሚወርዱት በፈቃድ፣ በህመም፣ በጡረታ ወይም ቅሬታ ካለ ቅሬታው ለምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ ቀርቦ አስፈላጊው ማጣራት ከተደረገ በሁዋላ መሆኑን ቢደነግግም፣ በቅርቡ ስልጣናቸዉን ያጡት አቶ ታደለና አቶ ሰይድ ከስልጣን እንዲወርዱ የተደረገበት አካሄድ ግን የክልሉ ምክር ቤት አዋጅ ከሚደመግገዉ ዉጭ መሆኑ ታዉቋል። አቶ ታደሰን በህገወጥ መንገድ ተክቶ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሆኖ የተሾመዉ ግለሰብ በኦህዴድ አመራር አባልነቱ የሚታወቅና ከገዢውን ፓርቲ ከህወሀት/ኢሀዴግ ጋር የቅርብ ትስስር ያለዉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁን የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ዳኛ በስልክ አንደተናገሩት የአዲሱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዳንት ሹመት "ህዝብን መናቅና ህዝብ ምን ያመጣል" በሚል ንቅት የተደረገ መት መሆኑንና "ትናንት ድርጅቴ ኢህአዴግ እንዲህ አድርጎአል እያሉ በሚዲያ ሲናገሩ የነበሩ ሰው ዛሬ ፍትሀዊ ዳኝነት ይሰጣሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም" በማለት ዳኞች ሃላፊነታቸውን እየለቀቁ ከመሄድ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌላቸዉ አስረድተዋል።

## በኢትዮጵያ ሙስና ብሄራዊ ባህል ሆኗል፣ ይህም የዘራፊው ወያኔ ስርዓት ልዩ የሆነ መገለጫ መሆኑ ተዘገበ

የወያኔ ዘረኛ ስርአት አቀንቃኝ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ባወጣው ጽሁፍ በኢትዮጵያ ሙስና ብሄራዊ ባህል ሆኗል፣ ይህም የስርዓቱ ልዩ መገለጫ ሆኑአል በማለት ዘግቡአል። ጋዜጣው እንዳለው ቀደም ባለው ጊዜ የተወገዘና ወንጀል የነበረው ጉቦ መቀበል ዛሬ የማያሳፍርና የስርዓቱ ሰዎች የቀን ተቀን ተግባር ነው።ይልቁንም ጉቦ አለመቀበል እንደ ጅል የሚያስቆጥር ምግባር ሆኗል ብሉአል።

ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ ጥቂት በንጽህና የሚሰሩ ባለስልጣናት በሌቦቹ ተውጠው የሌቦች መንግስት ይቋቋማል ያለው ሪፖ ርተር ይህ ደግሞ በአሁኑ ወቅት አቅጣጫው የጠፋውን ዘረኛ የወያኔ ቡድን ሞት እንደሚያፋጥነው በተዘዋዋሪ አስረድቷል።
ኢህአዴግም መንግስቱም መስቀለኛ መንገድ ላይ ናቸው፤ የቱ እንደሚሻላቸው መርጠው ሊጓዙ ይገባል ያለው ሪፖርተር ከሌቦ ች፣ ከሙሰኞች፣ ከከሃዲዎችና ከወንጀለኞ ጋር አብረን እንጓዝ ካሉ ጉዞው ወደ ገደልና ውድቀት ነው፤ መጨረሻውም ሌቦች የበላይነት የሚይዙበትና የሌቦች መንግስትየሚቋቋምበት ይሆናል ሲል ለማስጠንቀቅ ሞክሯል።

በዚህ ጉዳይ አስተያየት እንዲሰጡ የጠየቅናቸው አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል በበኩላቸው ይህን ጉዳይ ዛሬ የወያኔ አይቀሬ ሞት እየቀረበ ሲመጣ የስርዓቱ ተቆርቋሪ ሪፖርተር አነሳው እንጂ፣ እኛ ድሮ ገና ስንለው የነበረ ነው። ይህም ሆኖ እኔ ከሪፖርተር ጋር ልዩ ነት አለኝ ይኸውም ሙስና አሁን የመጣ የጥቂት ባለስልጣናት ጉዳይ ሳይሆን የስርዓቱ ዓይነተኛ ባህሪ ነው፤ሙስና ገንዘብ መዝረፍ ብቻ ሳይሆን በዘመድ መስራትን፣ ፍትህ ማዛባትን፣ ያለ አግባብ መበልጸግንና ሌሎችንም የሚጨምር ውስብስብ ጽንሰ ሃሳብ ነው፤ እነኚህ ብልሹነቶች ደግሞ የወያኔ ኢህአዴግ ብቸኛ መገለጫዎች ናቸው። ለአብነት ኤፈርት የሚባለውን ድርጅት መውሰድ እንችላለን፣ ወያኔ ገና ከጠዋቱ ይህንን ግብር የማይከፍል፣ ኦዲት የማይደረግ፣ የባንክ ብድር የማይከፍል ድርጅት አቋቁሞ ህዝቡን በመዝረፍና የንግድ ስርዓቱን በማናጋት መንግስታዊ ሙስና ሲፈጽም የኖረ ነው። ዛሬም እየፈጸመ ነው። ወደፊትም ይፈጽማል። ምክንያቱ ደግሞ የህልውናው መሰረት የተጣለው በሙስና ላይ መሆኑ ነው። ስለዚህ ሪፖርተር እንደሚለው በጥገና ለውጥ የሚመጣ ልዩ ነት የለም። ብቸኛው መፍትሄ የስርዓቱ ሙሉ በሙሉ መወገድ ነው በማለት አብራርተዋል።

## የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል የትግል ሜዳ መሃል አገርን ጨምሮ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በንዲህ እንዳለ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል መመስረት ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ መግባቱና፣ የዘረኛነት አባዜ መርዙን በመርጨት ስራ ላይ መጠመዱ ትግራይ ኦን ላይን በመባል በሚታወቀው ድረ ገጽ ላይ ባወጣው ጽሁፍ ገልጹአል። የዚህን የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል መመስረት ተከትሎ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ዲሴምበር 22 ቀን በዚሁ ድረ ገጽ ላይ የወጣው ጽሁፍ እንደሚያመለክተው የግንቦት 7 ሃይል በተለይም በትግራይ ህዝብ ላይ ለመዝመት የተነሳ ሃይል ነው ያለ ሲሆን፣ የትግራይ ህዝብ እሰከ አፍንጫው ድረስ በጦር መሳሪያ የታጠቀ፣ የተደራጀና፣ ወታደራዊ ስልጠናም የወሰደ በመሆኑ ይህን የግንቦት ሰባት ሃይል እሰከ ደም ጠብታው ድረስ ይፋለመዋል፣ ካለ በሁአላ የትግራይ ተወላጆች ይህን ሃይል እንዲፋለሙ ጥሪ አቅርቡአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በትግራይ ህዝብ ስም መነገድ የጀመረው ገና ወደ ስልጣን ወምበር ከመምጣቱ ቀደም ብሎ እንደነበር በሰፋት የሚታወቅ ሲሆን፣ በተለይ ደግሞ የስልጣን ወምበርን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ወዲህ የትግራይን ህዝብ ከሌሎቹ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቹና እህቶቹ የመነጣጠልና እርስ በርስም ጥላቻ እንዲፈጠር በማድረግ ስራ ተጠምዶ እንደቆየ በሰፋት ሲዘገብ መቆየቱ አይዘነጋም።

ይህ የመከፋፈል አባዜ የተጠናወተው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ አሁንም፣ ይህን ርካሽ ስልቱን በመጠቀምና የትግራይ ተወላጆችን ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ነጥሎ በማውጣት እስካፍንጫቸው የታጠቁና በወታደራዊ ስልጠናም ብቃት ያላቸው በመሆኑ እስከደም ጠብታ ይፋለማሉ በማለት መርዘኛ ፕሮፓጋንዳውን መንዛቱን ቀጥሉአል።

## የመለስ ራዕይ የሚባል ነገር የለም ሲል ስብሐት ነጋ

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ከኡራኤል ቤ/ክ እስከ ፍትህ ሚኒስቴር የመኪና መንገድ አካፋይ መሃል ላይ በግምት በ30 ሜትር ልዩነት ተደርድረው የነበሩ የዘረኛው መለስ ፖስተሮች እንዲነሱ ተደርጓል።

ስለጉዳዩ አስተያየት የተጠየቀ አንድ የአዲስአበባ ነዋሪ ኢህአዴግ በተለይ የመለስ ራዕይ በሚባለው ጉዳይ እጅግ ተጃጅሎ ከርሟል፡፡ ስንትና ስንት ችግር ባለበት ደሃ አገር በሚሊየን የሚቆጠር ብር ለመፈክር መጻፊያ ፖስተር የመንግስትና የሕዝብ ገንዘብ ሲባክን መክረሙ እጅግ የሚያሰዝንና የሚያሳፍር ነው ማለቱን ኢሳት ዘግቡአል።

የፖስተሮቹ መነሳት፣አለመነሳት ለእኔ ትርጉም የለውም የሚለው አስተያየት ሰጪው የግንባሩ ካድሬዎች ቀድሞውንም መፈክር በመጻፍ ሥራ የተጠመዱት የሕዝብ ድጋፍ ያገኙ መስሎአቸው የነበረ ሲሆን ሕዝቡ ግን በአድራጎታቸው ማፈሩን ሲረዱ ከፍተኛ ገንዘብ ያወጡበትን ምስል በሚያዋርድ መልኩ እየነቀሉ ለመጣል አላመነቱም ሲል ትዝብቱን መግለጹን ኢሳት አያይዞ ዘግቡአል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org